# ጭንነት የከበዳት አህያ

በተፈጥሮ ደካሞች እራሳቸውን ደካማ ነን ብለው አይጠሩም፣ እንዲያውም በተቃራኒው ታታሪና ሠራተኛ እንደሆኑ ሲተርኩ ነው የሚሰማው፣ በአንፃሩ ግን ይህ ነው የሚባልና የሥራቸውን ውጤት የሚያስመሰክሩበት አንድም አይነት በዓይን የሚታይና በእጅ የሚዳሰስ መረጃ ማቅረብ ባለመቻላቸው፣ (ባለመቻል ብቻም ሳይሆን ስለሌላቸው) የዚህ የባዶነት ውጤታቸውን ዘወትር የሚሸፍኑት ውጤት አልባ የሆነውና በእቅዳችን መሰረት መራመድ ያልቻልነው እኮ ሌሎች አላሰራ ስላሉን ነው በማለት ድኩማንነታቸውን የሸፈኑ እየመሰላቸው በእርግማንና በመኮነን ይበልጥ እራሳቸውን ሲያጋልጡ ማየት የተለመደ ቲያትር እንደሆነ ያላወቀና ያልሰማ ካለ እንድታውቁት ይሁን እላልሁ። ያድርባዮች፣ ያቋም የለሾችና የወሬ ሹሩባ ቆናኞች፣ የዛሬ ወፍ ዘራሽ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ነን ባዮች፣ ወይንም ደጋፊ አባል ነን በማለት አረፋ እስኪደፍቁ እንደባለዛር ሲያጓሩ የሚደመጡት ባዶ መናፍቃን ባደረጉት ጥልቅ ምርምር የደረሱበት የሜሌሊየሙ አዲስ ግኝታቸው እንደሆነ እኔና እኔን መሰሎች ያልነው ሳይሆን እራሳቸው የባለዛሮቹ አሚናዎች በራሳቸው ላይ የመሰከሩት ነው።

በተደጋጋሚ ከነዚህ የምዕራባውያንና በአፍሪካ የምዕራባውያን ታማኝ ሎሌ በመሆን ቀዳሚነቱን የያዘውን የወያኔ አገዛዝ ጫማ ስር የሚርመሰመሱ፣ ብዙሀኑን ውኀንብር ውስጥ በመጨመር ታላቅ ጸረ አንድነትና ጸረ ኢትዮጵያ ደባ በስውር በመፈጸም በእናት ሐገራችን ላይ ወደር የማይገኝለት ባለፉት ታሪካችንም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ለባዕዳንና በማደር ጸረ ኢትዮጵያ ለሆኑ አገር በቀልም ሆነ ከታሪካዊ ጠላት ጋር በመዳራት ለሐገራችን ውድቀትና ጥፋት ባለመታከት የሚለፉና የሚደክሙ በአምሳል የሰው ፍጡር የሚመስሉ በተግባራቸው ግን ከተራብ ጅብ የሚመሳሰሉ አይምሯቸው በስልጆ የተመረገና በሆዳቸው ብቻ የሚያስቡ ናቸው።

እነዚህ ቅሎች፣ ቅልነታቸው ለራሳቸውም ስለማይታወቃቸው ብዙውን ጊዜ ለራሳቸው ካላቸው የተሳሳተ ግንዛቤ በመነሳት ዘወትር ከአለት እየተላተሙ በየጊዜው ሲፈረካከሱና ሲሰነጣጠቁ ማየት የዘመናችን አሳዛኝ ድራማ ከመሆኑም በላይ በተደጋጋሚ የሚታይና የማይታረምም ክስተት ከሆነ ውሎ አድሯል።

በመሰረቱ እነዚህ እራሳቸውን እንደ ሰሜን ተራራ አሳብጠው የሚመለከቱ ነገር ግን በተጨባጬና እውነታው እንደሚመሰክረው ምስጥ ከቀለለው ኩይሳ በእጅጉ ያነሱ አሳዛኝ ወናፎች ናቸው። በተደጋጋሚ በተገኘ አጋጣሚ ሁሉ ለምን አንድ ስንዝር ወደፊት መጓዝ እንደተሳናቸውና ይልቁንም እርምጃቸው ከስንዝር ማነስ በከፋ የኋሊት እንደሆነ ሲነገራቸው የራሳቸውን የችሎታ ማነስና ብቁ አለመሆን አድበስብሶ ለማለፍ ዘወትር በተለመደውና ቂጣ በቀደደው አፋቸው "<u>ኢሕአፓ አላሰራ አለን</u>" በማለት እንደሞኝ ዘፈን ዘለዓለም "<u>የዓይኔ አበባ</u>" እያሉ ሲያላዝኑ መስማት እጅ እጅ ያለና ዘመን የሻረው፣ የመሸበት የቂሎችን መንደር ተሻግሮ መውጣት ያልቻለ ተረት ተረት ወይንም የተቃጠለ ፊልም እንደሆነ የሚነግራቸው ያጡ ስለመሰለኝ ልነግራቸው ተገድድሁ።

እነዚህ በራስ መተማመን የሚባል ነገር ያልተፈጠረባቸው ብቻ ሳይሆኑ በራስ መተማመን የሚለውን ቃል ሰምተውት እንደማያውቁም በእርገጥኝነት መናገር ይቻላል፣ ይህንንም ስል በሙሉ ልብነትና እምነት እንደሆነ አስምሩልኝ። አንድ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ በራሱ የሚተማመን ከሆነና ማድረግ የሚፈልገውንም ለማድረግ ብቃቱ አለኝ ብሎ ካመነ፣ በተለይ ብዙሀኑ ይቀበለኛል ወይንም ይደግፈኛል ብሎ ካመነ ስኬታማ መሆን ሲያቅተው በሌላው ላይ ጣትን በመቀሰር "እኔ ሰርቼ ነበር ነገር ግን እሱ ወይንም እነሱ አደናቀፉኝ" ማለቱ ወንዝ የማያሻግር የቱሪናፋዎች እዬዬ ሚዛን የማይደፋ ተራ ቅራቅንቦ ስለሆነ የተሻለ ሰበብ የሚያስጨብጣችሁ አስለቃሽ (ሙሾ አውራጅ) መቅጠሩ ጊዜ ልትሰጡት የማይገባ አጣዳፊ አጀንዳ ብታደርጉት ይበጃችሁ ይሆናልና አስቡበት እላልሁ ።

እነዚህ የአዞ እንባ የሚያነቡ ፍሬ ከርስኪዎች እንደገና ተገልብጠው "ኢሕአፓ የሚባል ድርጅት የለም"፣ ኢሕአፓ ሞቷል፣ በማለት እንደገና እራሳቸው የተናገሩትን መልሰው ሲያፈርሱት ይታያሉ፣ እውን እነዚህ ድኩማን የለም፣ ሞቷል የሚሉት ድርጅት አላሰራ አለን ብለው ሲወቅሱ "ባንድ እራስ ሁለት ምላስ" አይሆንባቸውምን? በውን የሚናገሩትን ያውቃሉ ብሎ ለመናገር አያስደፍርም። እንደአባባላቸውም የሞተ ድርጅት አላሰራ አለን ካሉ ያልሞተና ህይወት ያለው ድርጅትስ ቢገጥማቸው ምን ይሉ ይሆን? ይህንን ለመመለስ ለአወቀና ለተመራመረ ይከብዳል፣ ይህንን ለመመለስ እንደነሱው ድፍንና ቅል መሆንን የጠይቃልና፣ አይምሮ ያላቸው ይህንን እንዲመልሱ አይጠበቅም።

በማጠቃለያ ለነዚህ ምስኪን የዘመኑ ጭፍኖች እንደ እየሱስ ክርስቶስ "የሚሰሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ከማለት የተረፈ ሌላ የተሻለ አባባል ላገኝለት አልቻልኩም፣ ባይሆን ለትግል የተዘጋጁ፣ የትግልን መራራነትና ሊወስድ የሚችለውን ጊዜ መገንዘብ የተሳናቸው፣ አብዛኞዎቹ የወያኔ የቅርብ ጊዜ ሸንኮራ አገዳ የነበሩና ተመጥጠው የተተፉ፣ ገሚሱ የደርጉ የቀበሌ አብዮት ጠባቂና የደርጉ እንባ ጠባቂዎች በአንድ ወቅት በባዶነታቸው የተነሳ ንፋስ እንዳንሳፈፈው ፊኛ በተጨባጭ ሳይሆን በልባቸው ሳማይ ደርሰው የነበሩ ደናቁርቶች ናቸው። እነዚህ ሳይንሱ ያልገባቸውና የፖለቲካው ሀሁ ሊገባቸውም የማይችል ደነዞች ሲሆኑ፣ ትላንት ተፈጥረው ዛሬ የከሰሙ፣ ነገ ዘጠኝ ትንንሽ የሚወጣቸው ከነገ ወዲያ ደግሞ አርባ አራት ቢሁኑ ሊደንቀን የማይገባ ስለሆኑ አሁንም በድጋሚ "የሚሰሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ከማለት አልቦዝንም። በተጨማሪም ያንጎል እከክ የወረሰውን የገላ እከክ የያዘው ይመስል ለማዳንም ሙከራ አላደርግምና ይቅርታ ይደረግልኝ።

ጭንት እንደከበዳት አህያ በየሜዳው ከሚያንዛርጥ የዘመኑ ፖለቲከኛ ይሰውረን።

ዳመናው